ህዳር 24 ቀን 2004 ዓ.ም.

# መኢአድ በአሰብ ወደብ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ውይይት አካሄደ።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ህዳር 24 ቀን 2004 ዓ.ም. አዲስ አበባ በሚገኘው ዋናው ጽ/ቤት በአሰብ ወደብ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት አካሄደ።

በአሰብ ወደብ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ትምህርት የሰጡት የቀድሞው የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ከፍተኛ አመራርና የውጭ ግንኙነት ኃላፊ በመሆን ያገለግሉ የነበሩት ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም ናቸው።

ዶ/ር ያዕቆብ በትምህርታቸው ላይ  አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ምንሊክ፣ ንግሥት ዘውዲቱ፣ አፄ ኃይለሥላሴና የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አሰብ የኢትዮጵያ አካል መሆኗን ተገንዝበው ያካሄዱትን ትግል አስረድተዋል። አያይዘውም ወደብ ለአንድ ሃገር እጅግ ጠቃሚ መሆኑን የተለያዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ ተንትነዋል። ዛሬ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሃገር እንድትሆን በመገደዷ ለጂቡቲ ወደብ በቀን 6 ሚሊዮን ያህል ዶላር እንደምትከፍልና ይህ ገንዘብ ድህነትን ለማስወገድ ይችሉ የነበሩ በየዓመቱ ለሃያና ሰላሣ ፋብሪካዎች ወይም መጠነ ሰፊ ለሆነ ሰፊ የልማት ግንባታ ሊውል ይችል እንደነበረ አስገንዝበዋል።

በማይጨው ጦርነት ጊዜም አባቶቻችን ድል የሆኑት ኢትዮጵያውያን ወኔ ከድቷቸው ሳይሆን በወቅቱ ሃገራችን በጅቡቲ በኩል የጦር መሳሪያ እንዳታስገባ ፈረንሳይ በመከልከሏ ጥቃት እንደደረሰባትና ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ወደብ አልባ በመሆኗ እንደሆነ ተናግረዋል።

ዶ/ር ያዕቆብ ወደብ አልባና ወደብ ያለው በሌላ በሁሉም ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት አገሮችን የእድገት ሁኔታ በምሳሌነት በመውሰድ ወደብ አልባው አገር በኢኮኖሚ እድገቱ በ1ፐርሰንት ወደብ ካለው አገር ወደኋላ እንደሚቀርና ወደብ ያለው አገር በ24 ዓመት ውስጥ ኢኮኖሚው በእጥፍ ሲያድግ ወደብ አልባው አገር ግን ኢኮኖሚው በእጥፍ እንዲያድግ 36 ዓመት እንደሚፈጅበት ምሁራን በጥናታቸው ያሳዩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

አረቦች ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ብቸኛ የቀይ ባህር ተቀናቃኛቸው የነበረችውን ኢትዮጵያን ከባህሩ አካባቢ አግልለው ቀይ ባህርን የአረብ ባህር ለማድረግ የነበራቸውን ምኞታቸውን ማሳካታቸውንም ጨምረው ገልጸዋል።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ኢትዮጵያና ኤርትራ በታሪክ፣ በጀግራፊያዊ አቀማመጥ፣ በህዝብ አሰፋፈር፣ በዘር ያላቸውን ትስስርና በተለይም የኢትዮጵያን ተገቢና ሕጋዊ የባህር በር ጥያቄን አጢኖ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል ማድረጉን

አውስተው ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ደግሞ የኤርትራ ፓርላማ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ በሙሉ ድምፅ በመወሰኑ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድዋን በትምህርታቸው አስገንዝበዋል። ነገር ግን ሻቢያና ህወሃት ባደረጉት ያላሰለ ትግል ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ሲያደርጉ ኢትዮጵያ ከባህር በሯ ከአሰብ እንድትለይ መደረጓንም የዕለቱ መምህር ጨምረው አስረድተዋል። በኤርትራ መገንጠል ምክንያትም የአፋር እህቶቻችንና ወንድሞቻችን አለፈቃዳቸው ሁለት ቦታ መከፈላቸውን ጠቅሰዋል።

በ1992 ዓ.ም በኤርትራና በኢትጵያ መካከል በተካሄደው ጦርነት ኢትዮጵያ ድልን እየተጎናፀፈች ወታደሮቻችን አሰብ ለመድረስ ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ሲቀራቸውና ኤርትራንም አንዳንድ ግዴታዎችን ማስገባት እየተቻለ ባለበት ሁኔታ ጦርነቱን እንዲያቆሙ የህወሃት መሪዎች ማዘዛቸውን እንዲሁም በቀጣይ ወደ አልጀርስ ለድርድር ሄደው ስለባህር በራችን አሰብ ምንም አለማንሳታቸው ኢትዮጵያን በእጅጉ የጎዳ ሁኔታ መሆኑን ዶ/ር ያዕቆብ በአቀረቡት ትምህርት አብራርተዋል።

ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም እነዚህንና ሌሎችን በርካታ ነጥቦች ካብራሩ በኋላ በመፍትሔነት ሁለት ሃሳቦችን ሰንዝረዋል። እነዚሁም÷

1. የአሰብ ኢትዮጵያዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ኤርትራ የእርሻ መሬት እንደሚያስፈልጋት ሁሉ ኢትዮጵያም የባህር በር ያስፈልጋታልና ከኢትዮጵያ መሬት ላይ ለኤርትራ የተወሰነ የእርሻ መሬት በመሥጠት አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንድትሆን ብትደረግ ካሉ በኋላ ሌላውንም አማራጫቸውን እንደሚከተለው ገልጸዋል።
2. ኤርትራና ኢትዮጵያ አሰብን ከነደሴቶቿ በጣምራ እንዲያስተዳድሯት የሌሎች አገሮችን ተሞክሮዎች በመውሰድ መተግበር ቢቻል በማለት ትምህርታቸውን አጠቃለዋል።

በመቀጠልም የፕሮግራሙ መሪና አወያይ የመኢአድ የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሰቢ ወጣት ጌታቸው አበበ መድረኩን ለተሳታፊዎች ክፍት በማድረግ የተለያዩ ጥያቄዎችንና አስተያየቶች ተቀብለዋል። በዚህ መሠረትም በትውልድም በዜግነትም ኤርትራዊ የሆኑ አንድ አስተያየት ሰጭ ዶ/ር ያዕቆብ መፍትሔ ያሉት ሃሳብ በፍፁም ሊሰራ አይችልም ካሉ በኋላ ምክንያቱን ሲገልጹም የኤርትራ ልጆች ከህፃንነታቸው አንስቶ ኤርትራና ኢትዮጵያ የተለያዩ አገሮች እንደሆኑና ኤርትራ አሰብና ምጽዋ የተሰኙ ሁለት ወደቦች እንዳሏት እየተማሩ በማደጋቸው ተግባራዊ የማይሆን ሃሳብ በመሆኑ ሌላ መፍትሄ መፈለግ ይሻላል ብለዋል።

ሌሎች አስተያየት ሰጭዎች ግን አሰብ የኢትዮጵያ መሆኗን ታሪክ እንደሚመሰክርና ምንም እንደማያጠራጥር እንዲሁም ኢትዮጵያ ወደፊት ትልቅ አገር እንደምትሆን ራዕይ እንዳላቸው፣ ሻብያና ወያኔ እርስ በርስ ተመሰካክረው ኢትዮጵያን ያለባህር በር ማስቀረታቸውን፣ ህዝበ ውሳኔ አሰጣጡም ‹‹ባርነት ወይም ነፃነት?›› በሚል ፍፁም ፍትሃዊነት በጎደለው መልኩ የቀረበ መሆኑን፣ የአሰብ ወደብ በአሁኑ ወቅት ክፍት አጀንዳ እንዲሆን የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት እንደሚገባ ለምሳሌም የህዝብ ድጋፍን አሰባስቦ ፔትሽን አስፈርሞ ማቅረብ፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል አሁን ያለውን የድንበር አከላለል ለማስቀየር ዕውነቱን ለዓለም ለማስጨበጥ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደሚያስፈልግ፣ ለኤርትራ ወገኖቻችን ፍቅርን ማሳየት እና ሌሎችም ሃሳቦች ተሰንዝረዋል።

የመኢአድ ፕሬዚዳንት ክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል አሰብ በማያጠራጥር መልኩ የኢትዮጵያ አካል የነበረች መሆኗን ታሪክ በማጣቀስ አጠንክረው አስረድተዋል። ባንድ ወቅት ከኸርማን ኮሆኸን ጋር መጫወታቸውን አንስተው ኮኸን የህወሃት ሰዎች ዲሞክራት ይመስሏቸው እንደነበረና ነገር ግን ሥልጣን ከመያዛቸው ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ ኮኸን ለንደን ላይ ሻቢያን፣ ህወሃትን፣ ኦነግንና ደርግን ሲያደራድሩ አቶ መለስ ኢትዮጵያ የባህር በር አያስፈልጋትም ብለው መናገራቸው ያስደነገጣቸው መሆኑን እንደገለጹላቸው ተናግረዋል። አገዛዙ በህዝባችንና በሃገራችን ላይ እየፈጸመ ያለው በደል ከፍተኛ በመሆኑ ዛሬ ተደጋግፈንና በርትተን ልንታገለው ይገባል፤ ይህን ካላደረግን ግን የዘለዓለም ባርነት መርጠናል ማለት ነው ብለዋል።

ወጣት ጌታቸው አበበ የትምህርቱ አቅራቢ ዶ/ር ያዕቆብ በቅርብ ያስተሙት ‹‹<u>አሰብ የማናት</u>?›› የሰኘው መጽሃፋቸው ተሸጦ ገቢውን ብር 67,000.00 ለችግረኞች መስጠታቸውን ገልጸዋል። በመጨረሻም አወያዩ ዶ/ር ያዕቆብ መጽሃፋቸውን ሲያዘጋጁ ዓላማ ያደረጉበትን ዓቢይ ጉዳይ ማለትም ‹‹የዚህ ጽሁፍ ዋናው ዓላማ ታሪክን፣ ዓለም አቀፍ ህግን፣ የቀይ ባህር አፋሮች አንድነትና መብትን ከግንዛቤ አግብቶ … የአሰብ ጉዳይ እንደ አሁኑ በኢትዮጵያውያን አእምሮ እየተንቀለቀለ እንዲኖርና ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ ከዋነኛ ብሔራዊ አጀንዳነት እንዳይወርድ ለማድረግ ነው።›› ያሉትን በመጥቀስ የዕለቱን ውይይት አጠናቀዋል። በመጨረሻም የፕሮግራሙን ታዳሚዎች በመላው ኢትዮጵያ አንድነት መኢአድ ስም አመስግነው መርሃ ግብሩን ቋጭተዋል።

በውይይቱ ፕሮግራም ላይ የመኢአድ አባላትና ደጋፊዎች፣ የሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ ከተለያዩ ተቋማት የመጡ ተሳታፊዎች እና ሌሎችም ግለሰቦች የተገኙ ሲሆን በአሰብ ወደብ ላይ በጋለና ጥልቀት ባለው ሁኔታ ሰፊ ውይይት አካሂደዋል።